


የፊኒሽ TWR ተስፋ ለሴቶች ቡድን ተልዕኮ ሩጫ

ጸሎት

# እግዚአብሔርን ማመስገንና ሐሴት

አማርኛ

***“የእግዚአብሔር ሥራ ታላቅ ናት ደስ በሚሰኙበትም ሁሉ ዘንድ የተፈለገች ናት ሥራው ምስጋናና ግርማ ነው ጻድቁም ለዘላለም ይኖራል በታአምራቱ መታሰቢያን አደረገ “መዝ 110(111) ÷2-4***

ይህ አባባል በኛ ኑሮ ውስጥ ቢንፀባረቅ መልካም ነው ቁጭ ብለን በሕይወታችን እርሱ ያደረገውን ብናስብ ቀጥለን ደግሞ ብናመሰግነው መልካም ነው፡፡ የመዝሙር መጽሐፍ ጸሐፊ ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ ላይ የሚያስታውሰን በትክክል እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት መነሻ እንዲኖረን ያሳስበናል፡፡ መዝሙረኛው ፀሐፊ ምን ያሳስበናል? በምስጋና ተሞልተን እየዘመርን ሥራውን እስበን እንድናመሠግነው ያደርገናል፡፡ አምላካችንን በምህረቱና በድንቅ ሥራው ምንኛ የተመሠገነ ነው!

እግዚአብሔርን ልታመሰግን የምትፈልገው በምን ምክንያት ነው? ወደልብህ እየመጣ በደስታ እንድትሞላ የሚያደርግ የእግዚአብሔር ሥራ አለ? የተፈወስክበት? እንድትመቻች የተደረገልህ ነገር? እግዚአብሔር እንዴት እንደወደደህ? የተሰጠህን የሕይወት ነፃነት ይህን ሁሉ ስታሰበው ሥራው ብዙ ነው፡፡

ለማንኛውም የኛ ምስጋና ውስን አይደለም፡፡ የምድር ላይ ኑሮ በጣም የተወሣሰበና ከባድ ነው፡፡ በጣም ችግርና መከራ በሆነበት አካባቢ ስትሆን እስከ አሁንም የፀሎት ሥፍራን መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ በዚያ ሥፍራ ሠላምን እየሰጠ በተስፋ ይሞላል፡፡ በዚህ ወር ውስጥ እግዚአብሔር በተስፋ ለሴቶች ዓለም አቀፍ የሬዲዮ ፕሮግራም ጋር የሠራቸውን ድንቅ ሥራ እያሰብን የምናመሠግንበት ጊዜ ይሆናል በገጠር ውስጥ ያሉት የተስፋ ለሴቶች የፕሮግራም አዘጋጆች ብዙ የሚገልፁት ጉዳይ አላቸው፡፡ ይኸውም በፅሑፍና በቃላት የፀሎት ቡድኖችም ኅረቤቶቻቸውን እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ በተለይም በማረሚያ ቤት ያሉትን ታራሚዎች እያገለገሉ በተስፋ እንዲሞሉ እያስተማሩ እና እየፀለዩላቸው ነው፡፡ የእግዚአብሔር የቃሉ ዘር ደግሞ በአድማጮች ልብ ውስጥ እየተተከለ ይገኛል፡፡

ልክ እንደ መዝሙረኛው በደስታና በምስጋና በፊቱ እንዘላለን፡፡ ስለመልካም አፈጣጠሩ ስለጥበቃው ልናመሠግነው ይገባል የሱ ልጆች እንድንሆን በፍቅሩ ወደ ራሱ ስለጠራን የዘላለም ሕይወት ስለሰጠን ጌታን እናመሠግናዋለን፡፡

***“ምድር ሁሉ ለእግዚአብሔር እልል በሉ በደስታም ለእግዚአብሔር ተገዙ በሃሴትም ወደ ፊቱ ግቡ እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደሆነ እወቁ እርሱ ሠራን እኛም አይደለንም እኛስ ሕዝቡ የማሠማሪያውም በጎች ነን ወደ ደጆቹ በመገዛት ወደ አደባባዮቹም በምስጋና ግቡ አመሥግኑት ስሙንም ባርኩ እግዚአብሔር ቸር ምህረቱም ለዘላለም እውነቱንም ለልጅ ልጅ ነውና መዝ፡ 99(100) 1-5”***

twr WOMEN OF HOPE
**TWR Women of Hope Africa** • P O Box 4232, Kempton Park, 1620, South Africa
• +27 11 974 2886 • info@twrwomenofhopeafrica.org • twrwomenofhopeafrica.org

| | | |
|---|---|---|
| 1. የማዕከላዊ ኤሽያ ተማሪዎች በኖርዌይ ውስጥ የተስፋ ለሴቶች የፀሎት ቡድንን ስለተገናኙና አብረው መፅናናት ስለጀመሩ ጌታ ሆይ እናመሠግናለን በዚያ ሀገር የዚህ ፕሮግራም መሪና አስተባባሪ የሆነችው እህት በእምነትና በተስፋ እየሞላቻቸውና እያገለገለቻቸው ስለሆነ ስምህ ይባረክ አሁንም በበለጠ አጠንክራት፡፡ አሜን | 2. አምላካችን ሆይ በሩማኒያ ሀገር በፌስቡክና በሊሎችም ሚዲያዎች የሬዲዮ አገልግሎቱን የሚከታተሉ እየበዙ ስለሆነ እናመሠግናለን! በዚሁ ሚዲያ ደግሞ በተለያየ የትምህርት ደረጃ ላይ ያሉትን ሰዎች በስፋት ቃሉ እየደረሰ ስለሆነ አባት እግዚአህሔር ሆይ እናመሠግናለን! አሜን | 3. ጌታ ሆይ በቃልህ ላይ በተፃፈው መሠረት ስለድንቅ ሥራህ ለአዛብ እናውጃለንና ተባረክ ስምህንም በአሕዛብ መካከል እናውጃለን ታላቅና ድንቅ ነገርን በዚህ ዓመት አድርገህልናልና እናመሰግንሃለን፡፡ አሜን መዝሙር፡ 104(105)1-2 |
| 4. በታንዛኒያ ሀገር በአስር የሬዲዮ ጣቢያዎች የተስፋ ለሴቶች ሬዲዮ ፕሮራሙን ስለጀመሩ እንዲሁም በሚሰሙት በስህዋሊ ቋንቋ ቃልህ የአሕዛብ ጆሮ እየደረሰ ስለሆነ ጌታችን ሆይ እናመሠግንሃለን አሜን፡፡ | 5. አምላካችን እግዚአብሐሔር ሆይ በሮማኒያ በህዳር ወር ሊደረግ ያለውን የድራማ ፌስቲቫል አንተ እንደታሣካ እንድትከብርበት እንለምንሀለን በማረሚያ ቤት ውስጥ ቃልህ በግልፅ እንዲሰማና እንዲዳረስ ወደ አንተም ሰዎች እንዲመለሱ እርዳን ፕሮግራሙንም ባርክ፡፡ አሜን | 6. እግዚአብሔር ሆይ በኢንዶኔሺያ ውስጥ የሬዲዮ ስርጭቱ 46 ጣቢያ ስለደረሰ በጀቫንዝ ደግሞ 22 ስለደረሰ ለዚህ የሬዲዮ ስርጭት መስፋፋት እናመሠግንሀለን፡፡ ጌታ ሆይ የተስፋ ለሴቶች የሬዲዮ ስርጭት ደግሞ መላውን የኢንዶኔሺያ ሕዝብ እንዲደርስ አንተ ፕሮግራሙን ምራው! አሜን |
| 7. አምላካችን ሆይ በፊንላንድ ያለው የሚስዮናዊ ድርጅት በሕንድ ሀገር ላሉት ሰዎች ወንጌል እንዲደርስ በበጀት ላይ ብዙ እየሠሩ ነውና አንተ አግዛቸው በፊንሽ ሀገር ደግም ስለአንተ በግልፅ እንዲነጋገሩ ስለተፈቀደላቸው ነፃነት ኢየሱስ ሆይ ተባረክ እናመሠግንሀለን! አሜን | 8. እግዚአብሔር በአልቤኒያ ውስጥ ለተገፉት ሴቶች መጠለያ እተሰጠ ስለሆነ እናመሠግንሀለን እንዲሁም ደግሞ በክረምት ትምህርት ለመስጠት ሴት ልጆች ስውር ጥቃት በሚለው ድራማ በየካምፓቸው እየታየና የብዙዎችን ሕይወት እየለወጠ ስለሆነ እናመሠግንሀለን፡፡ አሜን | 9. አባት እግዚአብሔር ሆይ በዩክሬን ሀገር ወንጌል በስፋት እየተሰበከ ስለሆነ ብዙ እህቶች ደግሞ በማረሚያ ቤት በየቤታቸው እየሄዱ የተጎዱትን እያፅናኑ ስለሆነ እያመሠግንን አንተ ጉልበት እውቀትና ጥበብ እንድትጨምርላቸው ለነዚህ እህቶች እንለምንሀለን፡፡ አሜን |
| 10. ስምህ ከስሞች ሁሉ በላይ ስለ ሆነ እናመሠግናሀለን ስለ ታላቁ ስምህ ደግሞ ጉልበት ሁሉ ስለሚንበረከክ ኢየሱስ ሆይ እናመሠግንሀለን አሜን፡፡ ፊልጵ 2፡9-11 | 11. እግዚአብሔር በሴርቢያን ሀገር በመጋቢት ወር 2019 በተከፈተው የፀሎት ቡድን ውስጥ ብዙዎች ስለተጨመሩና እየተጨመሩ ስላሉ እጅግ እናመሠግንሀለን፡፡ ሸክም የበዛባቸው እህቶች ወደዚያ ፀሎት ስፍራ እየሄዱ እየተፅናኑ ስለሆነ እናመሠግንሀለን አሜን፡፡ | 12. ጌታ ሆይ በአፍሪካ ሀገር ብዙዎች ለዚህ በተስፋ ለሰቶች የአገልግሎት ቡድን እየታጩ ስለሆነ በዚህ ፕሮግራም ደግሞ ብዙዎች እየተገናኙ አብረው በመወያየትና በመፀለይ ብዙ መፍትሔ ካንተ ዘንድ እያገኙ ስለሆነ እናመሠግንሀለን አሜን፡፡ |
| 13. ጌታ ሆይ በተስፋ ለሴቶች የሬዲዮ አገልግሎት ፕሮግራም ተጠቅመህ በማረሚያ ቤት ብዙዎችን ወደራስህ እየመለስክ ስለሆነ ተመስገን ጌታ ሆይ ወዳንተ ለመጡት ለነዚህ አዳዲስ አማኞች ደግሞ የተመቻቸ ሕይወትና ኑሮ እንድትሰጣቸው እናመሠግንሀለን እንለምንሀለን አሜን፡፡ | 14. በፍራንስ ሀገር እጃቸውን ላንተ የሰጡትን ሴትና ወንድ ልጅ እንድታበረታቸው የተስፋ ለሴቶች የሬዲዮ አገልግሎትን ተጠቅመህ ትልቅ ሥራ እየሠራ ስለሆንክ እጅግ እናመሠግንሀለን ከዚህ በበለጠ ደግሞ ሰዎችን ወደ ቤትህ እንድትጠራ እንለምንሀለን አሜን፡፡ | 15. አምላካችን ሆይ በማላዊ ሀገር ለሥራህ በር እየተከፈተ ስለሆነ ከ200 ሴቶች ጋር ፀሎት እንዲያደርግ አንድ ፓስተር ስላስነሣህ እና መበለቶችንም የሚጎበኝ አገልጋይ ስላስነሣህ እጅግ እናመሠግንሀለን አሜን፡፡ |
| 16. ኢየሱስ ሆይ የሕይወት አለቃ ስለሆንክ ከአምስት ዓመት በኃላ መንፈሣዊ ሥራ በዙሪች እና በስዊዘርላንድ ሀገር መሰከረም 14-2019 እንደገና ስለተጀመረ እጅግ እናመሠግንሀለን በጠላት እጅ የተዘጋ ባንተ ኃይል ስለተከፈተ እናመሠግናሀለን አሜን፡፡ | 17. አምላካችን ሆይ አንተን ከተቀበልንበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ካንተ ጋር ስለተጓዝን ሥራችን ባንተ ስለተመሠረተ ባንተ ስለተጠናከርን በእምነታችን ፀንተን እስከ ዛሬ ስለቆምን በምስጋና በፊቱ እንሆናለን አባት ሆይ ተባረክልን አሜን፡፡ | 18. ተስፋ ለሴቶች የሬዲዮ አገልግሎት በታሚል ቋንቋ ስለተጀመረ አምላካችን ሆይ ተመስገን በዚህ በሬዲዮ የሚተላለፈው ትምህርት ደግሞ ለሕይወታቸው መሻሻያ እንዲሆን በመንፈስህ ማስተዋልን እንድትሰጣቸው እንለምንሀለን አሜን፡፡ |
| 19. የምንሰማው ቃልህ እውነት እና የምንታመንበት ስለሆነ ጌታ ሆይ ተመስገን አንተ የሰውን ሁሉ ሁለመና ታያለህ ሕዝቦችህ አንተን በሚጠሩበት ሰዓት በሁኔታዎች መሀል ጣልቃ ስለምትገባ እናመሠግንሀለን አሜን፡፡ | 20. አምላካችን ሆይ ሰዉር ጥቃት የሚለው የሬዲዮ ድራማ በኮሪያን ቋንቋ እየተዘጋጀ ስለሆነ በደቡብ ኮሪያ ያሉትን ሕዝቦች በወንጌል መድረስ እንዲቻል በአየር ላይ ቃሉን የሚቋቋም እንዳይኖር አንተ ብቻ ፕሮግራሙን ምራዉ ከደቡብ ኮሪያ ሸሽተው በቻይና ያሉትንም ኮሪያውያን ድረስላቸው በኢየሱስ ስም አሜን፡፡ | 21. አምላካችን ሆይ በካናዳ ያሉት የሴቶች የፀሎት ቡድንን ተጠቅመህ ብዙዎችን እያፅናና ስለሆነ እናመሠግንሀለን በበጎ ፈቃዳቸው የወርሃዊ የፀሎት ርዕሶችን አዘጋችተው ስለሚያስራጩትም ሰዎች እናመሠግንሀለን አሜን፡፡ |
| 22. በስዊድን ሀገር የሐና ካፌ በግል ተከፍቷል ጌታ ሆይ በዚህ ደግሞ የሕይወት ለውጥና የኑሮ መሻሻል ስለሚሆን እናመሠግንሀለን ለሌሎችም ተስፋን በሕይወታቸው የሚጭር ስለሆነ ተመስገን አሜን፡፡ | 23. አምላካችን ሆይ በፓርቱጋል ተስፋ ለሴቶች የሬዲዮ ፕሮግራም አድማጮችን እንድትለውጥ እየለመንን በዚህ ፕሮግራም ደግሞ ብዙዎች እየተባረኩ ስለሆነ እናመሠግናለን በኢየሱስ ስም አሜን፡፡ | 24. አምላካች ሆይ በፊትህ ያለነቀፋና ያለኩነኔ ስለተቀበልከን እናመሰግንሀለን ባንተ ፀጋ ነፃነትን ስላገኘን በመንፈስህ ሥር ስለሰደድን እናመሠግንሀለን አሜን፡፡ ኤፌ 1፡4-13 |
| 25. ትራንስ ወርልድ ተስፋ ለሴቶች 2020ዓ.ም በባጀት እጥረት ምክንያት ይዘጋል፡፡ እግዚአብሔር አምላክ የራሱ የሆነ ሌላ መንገድ እንዲያዘጋጅልን እንለምናለን፡፡ አሜን፡፡ | 26. አምላካችን ሆይ ሁልጊዜ ባንተ ደስተኞች ስለሆነ ሁሉጊዜ እኛ ደግሞ እናመሠግናሀለን ደስታችን ደግሞ በክርስቶስ በኩል ሙሉ ስለሆነልን እጅግ እናመሠግናሀለን በኢየሱስ ስም አሜን፡፡ ተሰ 5፡16-18 | 27. እግዚአብሔር በደቡብ ምስራቅ ሀገር በቬትናም እና በጃፓን ቋንቋ ተስፋ ለሴቶች የሬዲዮ ፕሮግራሞችን የሚያዘጋጁትን ስላስነሣ እናመሠግናሀለን አሜን፡፡ |
| 28. ጌታ ሆይ በጀርመን ሀገር ስውር ጥቃት በሚለው የሬዲዮ ድራማ በተለያየ የወረዳ ከተሞች ላይ ሊታይ ስለተዘጋጀ በዚህም መንገዳችን ስለከፈትክልን እናመሠግንሀለን አሜን፡፡ | 29. አምላካችን ሆይ የአለም አቀፍ የሬዲዮ ስርጭትና ኢ አር ኤፍ /ERF/ በጀርመን ለ60 ዓመታት አብረው ስለ ሠሩና በተለይም ኢ አር ኤፍ የተባለ መንፈሣዊ ድርጅት የተስፋ ለሴቶች ፕሮግራም በቅርበት እስከዛሬ ስለረዳህን እናመሠግንሀለን አሜን፡፡ | 30. ጌታ ሆይ ስለምንጠጣው ስለምንበላውና ስለምንለብሰው ጉዳይ ስለማንጨነቅና አንተ ራስህ አስበህ ስለምትሰጠን እናመሠግንሀለን የምንፈልገውን አንተው ራስህ አስበህ ስለምትሰጠን ተመስገን በኢየሱስ ስም አሜን፡፡ |